# ሞተች ገረዳቸው

ጥላቻን አውጆ ፣ ስርቆሽን ሰንቆ
ደም የሚያፈስበት ፣ እስካፍጫው ታጥቆ
በጨለጠው ውስኪ ፣ አረፋውን ደፍቆ
በስግብግብ አፉ ፣ በጎረሰው ታንቆ
በሙስና በክቶ ፣ ከደሃ ላይ ነጥቆ
አርፎ እንዳይቀመጥ ፣ የሰራውን አውቆ
ሞቱን ይጠብቃል ፣ አልሄደም ዕርቆ
በየጉራንጉሩ ፣ አለ ተደብቆ ።

ፍርድን እያዛቡ ፣ ትውልድ የበደሉ
የሰው ደም የጠጡ ፣ አገር የገደሉ
በግፍ አሰቃይተው ፣ አካል ያጎደሉ
ከውጡን በአንክሮ ፣ እየተከተሉ
ገፍቶ ስለወጣ ፣ አመፁና ትግሉ
ስላስደመማቸው ፣ ሕዝባዊ ማዕበሉ
እርስ በራሳቸው ፣ ሲወነጃጀሉ
ሞቱ አይቀሬ እንደሆን ፣ ስለተቀበሉ
በቁማቸው ሞቱ ፣ እህል እየበሉ ።

የተሰራው በደል ፣ መች ባንዴ ይረሳል
ገዳይ ተገዳዩን ፣ ሳያፍር ይወቅሳል
እንደተበደለ ፣ ያለቅሳል ይከሳል
ዛሬም አልጠግብ ባይ ፣ ቅርሻቱን ያገሳል
ወያኔም ሰባና ፣ ሾተሉን ይልሳል
ገዳይ ዘግይቶበት ፣ ሚች ይገሰግሳል ።

ሙሾ አውራጅ ይጠራ ፣ አልቃሽም ይቀጠር
አይጠፋም ይገኛል ፣ የሚችል ማቃጠር
ምንም ጠላት ቢሆን ፣ ተለቅሶ ይቀበር
 የሚያቀነቅኑም ፣ ሙሾ የሚያወርዱ
 አድር ባይ ከያኒ ፣ ዝቅ ያሉ የወረዱ
 ከህዝብ የተጣሉ ፣ ሙያውን የካዱ
አሉ የምናቃቸው ፣ ያዩ ፍርፋሪ
በሰው መቃብር ላይ ፣ ጎጇቸውን ሰሪ
ይምጡ ያስለቅሱ ፣ እንስማ ሲሉ እሪ ።

ሲያሽቃብጥ የኖረ ፣ አብሯቸው የገማ
እስቲ ካበላቸው ፣ ያልቅሱ በዜማ
እኛም እንያቸው ፣ ድምፃቸው ይሰማ
 ምነው ባፈሩ ላይ ፣ አወየው ወያኔ
 እጅም ተቆረጠ ፣ ፈሰሰልህ አይኔ
 ካንተ ተለይቼ ፣ ምን ሊውጠኝ እኔ
መች አወቅኩኝ እና ፣ እንደሆንክ ሃሳዊ
መስለኸኝ ነው እንጂ ፣ ዘለዓለማዊ
 አስከትለኝ እንጂ ፣ እንዴት እሆናለሁ
 አንተ ነህ ውበቴ ፣ መች ካንተ አምራለሁ
 የቀን ጅብ ወያኔ ፣ ጥራኝ ብዬሃለሁ
ብለው ያዚሙለት ፣ ካበላቸው ጌታ
እስቲ በተራቸው ፣ ይክፈሉ ውለታ
ከንግዲህ ለነሱ ፣ ስለማይኖር ቦታ ።

ይብላኝ ላጋፋሪ ፣ ይብላኝ ላድር ባዩ
የቀን ጅብን ያክል ፣ ማዕረግ ሳያዩ
አጋሰሶች ሆነው ፣ ነገን ስላላዩ
በፍርደ ህሊና ፣ ስለሚሰቃዩ
ከወገን ለራቁ ፣ ከህዝብ ለተለዩ ።

መሬት ተቀራማች ፣ የውጭ አገር ባንኮች
ደሃ የሚያስለቅሱ ፣ አጋሰስ በዝባዦች
ያለ ርህራሄ ፣ የሰው ደም መጣጮች
          ኢትዮጵያን ለነሱ ፣ ያረገች ፍሪዳ
          የወገኑ ጠላት ፣ አገሩን የከዳ
          ቀብሩ ስለሆነ ፣ ጥቁሩ ይሁዳ
ይምጡ ሙሾ ያውርዱ ፣ ባንዳዋ ሞታለች
ዳግም ላትመለስ ፣ ተሰነባብታለች
ባገሬ ወግ ባህል ፣ ቅበሩን ትላለች ።

እነሱም ያልቅሱ ፣ እንደየ ቋንቋቸው
ተዳፈነ ሞተ ፣ ብዝበዛ ህልማቸው
ለራሷም አልሆነች ፣ ያቺ አገልጋያቸው
ወያኔም ተሸኘች ፣ ሞተች ገረዳቸው
ጥገቷም ኢትዮጵያ ፣ አትታለባቸው ።

ላገር ቤት ባንኮችም ፣ ቢነገርም መርዶ
ሙሾ አውራጅ እንዳይቀጥር ፣ ካዝናቸው ባዶ
በልማት ስም ጥፋት ፣ የሌባ እጁን ሰዶ
የተራቆተ ነው ፣ ካዝናው ተቀዶ
አክስሮታል ቀድሞ ፣ ወያኔ አጋሚዶ ።

እንደምንም ብቻ ፣ ቅበሯት ገረዷን
ይሁን ብኳል ህዝቡም ፣ ወዶታል መሄዷን
እራሷን ገላለች ፣ ስታልም ሆድ ሆዷን
          እንግዲህ እርም ይሁን ፣ ስራዋም ይረሳ
          ታሪክ አጉድፋለች ፣ እራሷ ኮስሳ
          ታሪኳም ይቀበር ፣ ዝንተዓልም ትረሳ ።

ታዛቢው

july 4, 2018